# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና

# ትንበያ መጽሔት

## ከዲሴምበር 1-10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

## እንዲሁም ከዲሴምበር 11-20 እና ከዲሴምበር 21-31/ 2024

## የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ዲሴምበር 2024

አዲስ አበባ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ - 1 -

ምስል 1፡ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ - 2 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 3 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር1 እስከ 10/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት - 3 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ - 3 -

የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር - 3 -

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 4 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 4 -

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 5 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2024 - 5 -

ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 5 -

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 6 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከዲሴምበር 11-20, 2024 የሚኖረዉ ዝቀተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ - 6 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከዲሴምበር 11-20, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 6 -

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 7 -

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 7 -

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 8 -



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ

በዲሴምበር የመጀመሪያው አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ተስተውሏል፡፡ በተለይም የሰሜን ምሥራቅ፣ መካከለኛው፣ ምሥራቅ እና ደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ነበራቸው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ ከዕለት ወደ ዕለት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ጨምሮ የተስተዋለ ሲሆንና በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ሥፍራዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል። ለአብነትም በባህር ዳር 4.6፣ በደበረ ማርቆስ 2፣ በቢሾፍቱ 4.2፣ 4.2፣ 4.4፣ 3.8፣ 2.2፣ 3.1፣ በጅማ 4፣ 2.8፣ 4፣ በሮቤ 4.9፣ 4.6፣ 4.2፣ 3.4፣ በአዴት4.2፣ በአዲግራት 4.5፣ 4፣ በደብረብርሀን 2.2፣ 2፣ 0.2 0፣ -1.0፣ -1.6፣ -1.4፣ -0.2፣ 1.8፤ በሐሮማያ 4.4፣ 3.4፣ 2፣ 0.4 1፣ 0.8 1.8፣ 2፣ 1.8፤በአለም ከተማ 4.8፣ 4.2፣ 4፣ 4.2፣ 4፣ 3.8፣ 3.2፣ 4፤ በአምባማሪያም 3.6፣ 4፣ 3.6፣ 4.2፣ 4፣ 4.5፣4.5፣ 3.5፣ 4፤ በሮቤ 4.6፣ 4.2፣ 3.4፤በአርሲ ሮቤ 4፣ በባቲ 4.8፣ 4፣ 4.2፤ በቡኢ 4፣ 3፣ 4፣ 3፣ 3.6፣ 2፣ 2.5፣ 2.4፤በዳንግላ 2.5፣ 2፣ 4.5፤ በደባርቅ 4.5፣ 3.5፣ 3.5፣ 4፤ ደብር ታቦር 2.5፤ ደብረ ወርቅ 3.2፣ 2፣ 4፤በእነዋሪ 4.5፣ 2፣ 4.5፣ 4.5፣ 2.6፣ 3.5፣ 3.6፤በፊቼ 3.8፣ 3.2፣ 4.2፣ 4፣ 4፤በእምድብር 4.8፤ በጅግጅጋ 2፣ 2፣ 4.5፣ 4.6፣ 1.4፣ 1.2፣ 1.6፣ 1.2፣ 3፣ 1.8፤ በመሐል ሜዳ 1፣ 3.2፣ 2.5፣ 2.8፣ 0.2፣ 4.2፣ 4፣ 3፣ 2.5፤በሾላ ገቢያ 2.1፣ 1፣ 2.1፣ 2፣ 1፣ 2፣ 3፣ 2፣ 1፤ በወገል ጤና 4.5፣ 2.5፣ 3፣ 1.5፣ 1፣ 4.5፣ 2.5፤ እንዲሁም የትኖራ 4 በዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል 1)፡፡

በሌላ በኩል በጥቂት የምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በመጀመሪያዎቹ አራት ቀናት ቀላል መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል። ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው ጣቢዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በጋምቤላ 37.6፤ በጋቲራ 17.3፤ በአርጆ 11.4 እና 16.8 እንዲሁም በቻግኒ 8.7 እና 11.7 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ምስል 1፡ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ከፋ፤ ከኦሚያ ክልል ቄለም ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፤ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል፣ የካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከአማራ ክልል የምዕራብና የማዕከላዊ ጎንደር፣ የአዊ ዞን፣ ሰሜን ጎጃም፤ላይ ከ2-45 ሚሜ የሚደርስ ከ1-3 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጋምቤላ ክልል ፤ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ከፋ፤ ከኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፤ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል፣ የካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከአማራ ክልል የምዕራብና የማዕከላዊ ጎንደር፣ የአዊ ዞን፣ ሰሜን ጎጃም፤ ዞኖች መደበኛና በጥቂት ቦታዎች ላይ ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ፡፡ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው የሆኑት ከኦሮሚያ ክልል ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረናና ምስራቅ ቦረና፣ ባሌና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲና ምዕራብ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

አርሲ፣ የሶማሌ ክልል ዞኖች፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች በደረቃማው የአየር ሁኔታ ስር ቆይተዋል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር1 እስከ 10/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት አብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ ተስፋፍቶ ተስተውሏል። ይህም ሁኔታ የመኸር ሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበረ። በሌላ በኩል ከነበረው ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ጋር ተያይዞ በደጋማው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ የተጠናከረ ሲሆን በመስኖ በሚለሙ ሰብሎች፣ በጓሮ አትክልቶችና በፍራፍሬ ተክሎች እንዲሁም ቅዝቃዜን በማይቋቋሙ እንሰሳት ጤና ላይ መጠነኛ አሉታዊ ተጽዕኖ ነበረው።

በሌላም በኩል በአንዳንድ የምዕራብ ኢጋማሽ ኪስ ቦታዎች ላይ የነበረው መጠነኛ እርጥበት ለቋሚ ተክሎች አዎንታዊ ጠቀሜታ ነበረው (ካርታ 4)፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት የመካከለኛው አባይ እና ባሮ አኮቦ በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ መጠነኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ በሌላ በኩል አብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ ሁኔታ ስር እንደነበሩ የተተነተኑ የውኃ ሚዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ (ካርታ 5)፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከሳይቤሪያ ከፍተኛ የአየር ግፊት ላይ በመነሳት ወደ ሀገራችን የሚነፍሰው ደረቅ እና ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚስተዋል ሲሆን፤ የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በሰሜን ምስራቅ፣ በሰሜን፣ በምስራቅና በደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል( ካርታ 6)፡፡ በሌላ በኩል በጥቂት የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ አከባቢዎች ላይ የደመና ሽፋን የሚኖራቸው ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በምዕራብ፣ በደቡም ምዕራብ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከዲሴምበር 11-20, 2024 የሚኖረዉ ዝቀተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከዲሴምበር 11-20, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመጪዉ የዲሴምበር ሶስተኛዉ አስራ አንድ ቀናት ወደ ሀገራችን የሚነፍሰው ደረቅ እና ቀዝቃዛ አየር ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚስተዋል ሲሆን፤ የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በሰሜን ምስራቅ፣ በሰሜን፣ በምስራቅና በደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል ፡፡ በሌላ በኩል በጸሀይ ኃይል ታግዘው ከሚፈጠሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የደመና ክምችት ይኖራቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለይም በደቡብ ምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የሀገራችን ሶማሌ ክልል ደቡባዊ ክፍል፤ የጉጂ የቦረና ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገራችን ክፍሎች ላይ የሚኖረው ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ለመኸር ሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል። በሌላ በኩል ደረቃማ ከሆነው የእርጥበት ሁኔታ ጋር ተያየዞ በተለይም በሰሜን፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ፣ በመካከለኛዉና በደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በአንጻራዊ ሁኔታ የሚጠናከር ሲሆን ይህም ሁኔታ በቋሚ ተክሎች፣ በጓሮ አትክልቶችና በመስኖ በሚለሙ ሰብሎች እድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚኖረው ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታም በአነስተኛ የቤት ጤንነት ላይ መጠነኛ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊወን ቅድም ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። በሌላ በኩል በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት አካባቢዎቸ የሚኖረው እርጠበት በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበጋ ወቅት ሰብሎችም ሆነ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት በጎ ጎን ይኖረዋል።



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት አብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ደረቅ ሆነው እንደሚቆዩ የሚጠበቅ ቢሆንም በጥቂት ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት ያገኛሉ፡፡ መጠነኛ እርጥበት ከሚጠበቅባቸው ተፋሰሶች መካከል ባሮ አኮቦ፣ በመካከለኛ እና ታችኛው ኦሞ ጊቤና ስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ አይሻ፣ አፋር ደናክል፣ ኦጋዴን እንዲሁም መረብ ጋሽ ተፋሰሶች ደረቅ ሆነው የሚቆዩ ሲሆን፤ በተፋሰሶቹ የሚገኘውን ውሃ ብክነትን በቀነሰ አግባብ ጥቅም ላይ ማዋል ያስፈልጋል፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et